# ታሪኸኛ፥ከራሪት ሜሪ ኣርሚዴ፥እንክትዝከር

=====//////======//////======/////====

ክቡራትን ክቡራንን፥ብዛዕባ ከራሪት ሜሪ ኣርሚዴ ክጽሕፍ ካብ ዘድርከኒ ሓደው ኣብ ታሪኽ ዝግደስን ብዝዕለስን ዝቐለስን ታሪኽ ዝሓምምን ባእታ ብምኳነይ፡ዓቕመይ ዝፈቐዶ ንሪመይ እጃመይ ከበርኽት ንፈጣሪ ሓግዘኒ እናበልኩ፣እታ ዝክእላ ዝገብርን ክገብርን ዝፍትንን ሒለት ዝብልን ወከፍ'የ።በዚ መሰረት ድማ ብዛዕባ ደቀ እንስትዮ እሞ ድማ ታሪኽ ሰሪሐን ዝሓለፋን ኣብ ሕብረትሰብ ዝነበረ ዝተፈላለየ ወጽዓታት ንመጻኢ ወለዶ ከስተምህርን ንውሉድ ወለዶ ክመሓላለፍን ዓሊሙ፡ክጽዕት እፍትን'የ።

እንሆ ድማ ከም ኣሰር ምኩልኳለይ ድማ ብዛዕባ እታ ኣዚያ ታሪኸኛ ዝኮነት ከራሪት ሜሪ ኣርሚዴ ብኸፊሉ ናብ ኣንበብቲ ከምጽእ ዕድል ገይረ ኣለኹ እብል።

በሉ እምበኣር፥ብዛዕባ ሜሪ ኣርሚዴ ኣብዚ ቐረባ መዓልታት ኣብ ማሕበራዊ መራኸቦ ብዙሓት ብምቕራብይ፣ናብ ሰፊሕ ሕዝቢ ከቕርቦ ከምዘለኒ እኒ ብጻይናን ሓውናን ሰመረ ወልደማርያም ዝርከብዎም ሓሳብ ብምምጣዎም ይኹን ኣነ እውን ብምርዓመይ ናብ ሰፊሕ ኣንባቢ ክቐርብ እገብር ኣለኹ።

“ከራሪት ሜሪ ኣርሚዴ፡

በዓልቲ ሃበባ ከራሪት ሜሪ ኣርሚዴ፡ሕብራዊ ስእላ፡ ካብ ኢድ ክቡር ኣቶ ኪሮስ ወልደሚካኤል (ገዲም ቴክንሻን ሬድዮ ኢትዮጵያ ነበር) ሎሚ ቕነ ዝረኸብኽዎ'ዩ።እዞም ኣብ'ዚ ታሕቲ ዘለዉ ክልተ ሰባት ዝሓዘት ዘላ ስእሊ፣እቶ ኣቦ ኣቶ ኪሮስ ኢዮም፥እታ ኣደ ድማ ወ/ሮ ለምለም እያ።ስእልታትን ተዘክሮታትን ከራሪት ሜሪ ኣርሚዴ ዘለዎም፡ኣብ ፒያሳ ካብ ጥንቲ ጥቕምቲ ጎርባብታን ቀረብታን ዝነበሩ ኢዮም።




ታሪኽ ከራሪት ሜሪ ኣርሚዴ ብግቡእ ኣይተሰነደን ኣሎ።ተረኺቲ፣ከም ድልየቶም ድማ ይትርኽዎ ኣሎዉ።ከራሪት ሜሪ ኣርሚዴ ኣበይ ተወሊዳ፧ ትውልዳ ብልክዕ ኣበይ ኢዩ፧ ኣብ ታሪኽ ኢትዮጵያ ከም ሓንቲ ዉልቀሰብ መጠን፣ብርክት ዝበሉ ስማ ዘርቁሑ ፍጻሜታት ሰሪሓ ክነሳ ግን እቲ ናታ ታሪኽ ንካልኦት ይወሃበን ወ ይወሃቦም ኢዩ።ሓወልታ እኒ መን ኣሰሪሖሞ፧ ንምንታይ ከ ፈሪሱ ኣሎ፧ ኣበይ ኣሎ እቲ ሕመረት ሓወልቱ ኸ፧ ብዙሕ ሕቶታት ኣሎዉ ክምለሱ ዘለሎም እብል።

ቅድሚ 3 ዓመት ኣቢሉ መበል 100 ዓመት ዓመት፡ዕለተ ልደታ ኣድሂብና ገለ ክንገብር ሓሳብ ነይሩ'ዩ ግን ብዝተፈላለዩ ምኽንያታት ብፍላይ ድማ ሓቀኛ ታሪኻን ምስክርነት ዝህቡ ሰባትን ብቐሊሉ ምርካብ ከቢድ ብምንባሩ'ዩ፣ገለ ካብ'ቲ ምኽንያታት ኣብ ግቡእ ሰዓቱን ዕለቱን እቲ ዝሓሰብናዮ ክንገብር ዘይከኣልና ዝነበርና ክበሃል ይከኣል'ዩ።

ሎሚ ግን ድሕሪ ክንደይ ድኻም ንኣቶ ኪሮስ ወልደሚካኤል (ገዲም ቴክኒሻን ሬድዮ ኢትዮጵያን ታሪካዊ ሰብን)፣ንሳ ቕድሚ 65 ዓመት ሳዕስዒት ከም ዝመሃረቶም ባእታ ይኹን ካብ ኣስመራ ኳል 8 ዓመት ኮይና ናብ ከተማ ኣዲስ ኣበባ ፒያሳ ዝመጸት ወ/ሮ ለምለም ዊስኪ (በዓልቲ ብዘት) እሙናት ምስክራትን ይኹን ካልኦትን ብምርካብና ይኹን ጋሻ ስብሓት ገብረዝጋብሔር (በዓል ማይ-ምሻም) ደራስን ጸሓፍን ዘዕለለና ይኹን ዝሃበና ሓበሬታ መሰረት ብምግባር ይኹን ኣዘማዳ ካብ ዘለዉዎ ረኺብና፣ ኣብ ገለ ምዕራፍ በጺሕና ኣለና።

ሜሪ ኣርሚዴ ኣብ ዘመናዊ ሳዕስዒት፣ኣብ ክራር ዓለም ብፍላይ ደቂ ኣንስትዮን ሞያ ጽባቐ ጸጉሪ-ርእሲ ደቂ ኣንስትዮ ወሳንን ቐላስን ግደን ተራን ዘለዋ ጥራሕ ዘይኮነትሲ ታሪካዊት ሰብ ኢያ።

ኣብ ጊዜ ደርጊ ቀልዑት ከለና ጎረቤትና ወ/ሮ ምጽላል ግርማይ፣ቀልዑ ኣኪባ ይኹን ብፍላይ ህ ኢሉ ንዝሰምዓ ሰብ፣ ብዛዕባ ሜሪ ኣርሚዴ ኣድሂባ ተውግዓና ነይራ'ያ።ኣዴታትና ድማ ሓንቲ ኳል ኣንስተይቲ ኣብ ቕድሚ ሰብ ወይ 'ተጠሪጣ' ወይ ድማ 'ተፈስያ' ዘጋጥማ ዝነበረ ሕማቕ ባህልን ኣረኣእያን ከውግዓ ንሰምዕ ነበርና።ብፍላይ ድማ ሜሪ ኣርሚዴ ኣብ ሬድዮ ጣብያ ዝፍኖ ዝነበረ መደባት ይኹን ዜና ክቃላሕ ከሎ "ከመይ ሓዲርኹም፧" ክትብል ከላ እቲ ሰማዒ ድማ ካብ ዘለዎ ቦታ ትንስእ ኢሉ ካብ መቐመጭኡ ብድርግ ብምባል "እግዚአብሔር ይመስገን!" ይብል ምንባሩ ታሪኽ ይሕብረና ኢዩ።

ሜሪ ኣርሚዴ ድማ ሓደ መዓልቲ ሓፍ ኢላ "እግዚኣብሔር ይመስገን!" ክትብል ከይሓሰቡቶ ኣብ ቅድሚ ሰብ ኣተንፊሳ፣በዚ ሓፈራ ጠፊኣ ናብ ኣዲስ ኣበባ ከም ዝመጸት ማማ ለምለም ዊሰኺ ትማሊ ሰሉስ (ቅድሚ ሰሙን) ምስ ኣዕለለትና፣ናብ ድሕሪት ክምለስን ወድ ሰብ ሕጊ ተፈጥሮ ኮይንዎ ክፈስው ወይ ክጠርጥ ኣብ ዘይክእሉ ባይታ፣ንደቂ ኣንስትዮ ድማ ኣዚዩ ኣነዋርን ክዑብን ብምንባሩ እንሀት ከራሪት ሜሪ ኣብነት ኢያ።ካልእ ሓንቲ ጓል ድማ ኣብ ቕፍሚ ሰብ ብምጥራጣ ተሓኒቃ ከም ዝሞተት ቀልዑት ከላና ኣብ መጋርያ ዕላል ወለድና ንሰምዖ ዝነበርናሲ ዕላል ጥራሕ ዘይኩነሲ ሓቐኛ ፍጻሚ ምንባሩን ዝሕዝዝን ኣጋጣሚታት ይፈጥር ምንባሩ ሕያው ኣብነት'ዩ።



ንዓመታት ድማ ሓቀኛ ታሪኻን ድሕረባይትኣን ኣብ ጊዜ ጥልያን ብኸመይ ናብ ኣዲስ ኣበባ ከም ዝመጸት ይኹን ክራር ብኸመይ ከም ዝጀመረት ኣቦ ዜማ ሃገር ዘስመዩ፣ኣተውብርሃን ሰጊድ ካብ ሜሪ ኣርሚዴ ክራር እናወሰዱ ንክራር ከም ዝተዛመዱን ወዘተን ምስክርነትን ገለ ሰነዳትን፣ብዓቢኡ ሳላ ሳህልን ደገፍን ኣምላኽን ብግዱሳት ሰባት እውን ኣብዚ ደሓን ብርኺ ክነጽሕ ክኢልና ኣለና።

ሓደ ምዕልቲ ድማ ናብ ኣንበብቲ ክቐርብ ኢዩ እብል።"-ክቡራት ኣንበብቲ እዚ ኣብ ማሕበራዊ መራኽቦ ቀሪቡ ዝነበረ'ዩ።እንተኩነ ብሰፊሑ ድማ ጋሽ ስብሓት ገብረዝጋብሔር ቕድሚ 47 ዓመት ኣብ መጽሔት መነን ናብ ኣንበብቲ ብቛንቋ ኣምሓርኛ ኣሰፊርዎ ካብ ዝነበረ፣ነቲ ሰነድ ብምርካብ ይኹን ንሱ ብሕይወት ኣብ ዝነበረሉ ኣብ ፒያሳ ይኹን ኣብ ጨርቀስ ከባቢ ዘዕልለና ዝነበረ ብኸፊሉ ነዚ ዝስምዕብ ይመስል ኢዩ።

“እኔ መጀመሪያ አርቲስት ለመሆን የመረጥኩት ገና ትንሽ ልጅ ሆኜ ነው።የተወለድኩት አራዳ ጊዮርጊስ ነው።በሠፈራችን መደዳውን ጠጅ-ቤት ነበር።ዘውትር ይዘፈናል።እኔም የታዘዝኩትን ትቼ ወደ ዚያው ሄጄ ቀስ ብየ እያሾለኩ፣ በመጋረጃ ውስጥ እመለከታለሁ።የዚያን ጊዜ ዘፋኞቹ እነ ባፈና ወልዱ፥ንጋቷ ከልካይ፥እነ ጥሩ ብርቄ ነበሩ።

እነሱት በመመልከት ስሜት ያዘኛና አንጉራጉር ጀመር።ሰውም “ነይ እስቲ ሜሪማ ዝፈኝልን” ይለኛል።ያኔ ስሜ ሜሪማ ነበር። የአራዳ ሴቶች መሪ ከሆንኩኝ በኋላ ስሜን ሜሪ ብየ ቀየርኩት።አባቴ ጉንደሬ እናቴ ራያ ናቸው።እነሱ ናቸው ሜሪማ ብለው ስም ያወጡልኝ።


ሜሪ ከወዳጅዋ ከማዳም ኤልሳቤጥ ጋር ።

ይኼውልህ አርቲስት ለመሆን የነበረኝ ስሜት ከዚያን ጊዜ ነው የጀመረው።በጠላት ጊዜ እንኳ ምንም ልጅ ብሆን፥ ይባል የነበረውን ሁሉ አንጉራጉር ነበር።

ሜሪ አርሚዴ ፋቂ የሚባል ሀገር ሁለት ዓመት በሰደት ኖራለች።በኃላም የፋሽስት መንግስት“መኩሴዎች ፣ህፃናት፣ደካሞች ተመለሱ” ብሎ ሲያውጅ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰችና እዚያው ቀድሞ ሠፈሯ አራዳ ገባች።ሜሪ ስትናገር “ዘመዶቼ ሙያ እንዳውቅ በይ ፍትይ፥ ስፌት ስፊ” ሲሉኝ አሻፈረኝ እያልኩ ማንጉራር ብቻ ሆነ።ነጋ ጠባ እገረፋለሁ።እኔ ግን አንዴ በዚህ ተለክፌያለሁና ውሎየ ጠጅ-ቤት ሆነ።ቤተዘመድ ተሰብስቦ መከረና ሚሲዮኖች ዘንድ ሄጄ እንድማር ተደረገ።

እዚያም ሄጄ ትምህርቱ አልሆነልኝም።ማንጉራር ሆነና መምህራኑን አስቀጣቸው።በኃላም ይህቺ ልጅ ዘፈን እንጂ ትምህርት አይሆናትም፣ ደህና ልጆችን መጥፎ ትምህርት ታስተምርብናለች ብለው ትምህርት ቤቱን እንድለቅ አደረጉ። ዘመዶቼም ተናደው እንደገና እዚያው ትምህርት ቤት አንጠልጥለው ወሰዱኝና ጫጩትም ቢሆን እዚሁ ትምህርት ቤት ሆና ትጠብቅ እንጂ እቤት ውላ ጠባይዋ ሊሻሻል አይችልም ብለው የትምህርት ቤቱን አስተዳዳሪ ለመኗቸው።እርሳቸውም የቤተሰቦቼን መጨነቅ አይተው ለሁለተኛ ጊዜ ተቀበሉኝ።

ሜሪማ እንደሆንኩ አሁንም ሀሳቤ እዚያው ጠጅ ቤት ነኝ።ጓደኞቼ ከመፅሐፍ ጋር ሲታገሉ እኔ አንጉራጉራለሁ። የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ የነበሩት መነኩሴ ተበሳጭተው ሁለተኛ ዓይኗን እንዳላይ ብለው አባረሩኝ።የትምህርቴም ነገር በዚሁ አከተመ።

አራዳ ጊዮርጊስ ከሚገኙት ጠጅ ቤቶች ከሚገኙት ጉራ እያልኩ መዝፈኔን ቀጠልኩ።ከጊዜ በኋላ ከአንዲት ፈረንሳዊት ጋር ተዋወቀሁ።ከእርሷም ጋር ፍቅራችን የጠና ሆነ።በዘመኑ ብርቅ የነበሩትን ዳንሶች አጠናሁ። በዚሁ ሙያዬ ሰው ሁሉ ጉድ አለ።ያን ጊዜ በውስጥ ሱሪና በጡት መያዣ፥ በባዶ እግር ነበር የሚደነሰው።

ታዲያ ይህ ጉዳይ ሕብረተሰቡን አስቀጥቶት ነበር።ፈረንሳዊቷ ወደ ሀገሯ ስትገባ ንብረቷን ለኔ አስረከበችኝ።ከዚያም አሁን የሞዳኖቫ ሱቅ ከተሠራበት የራስ ኃይሉ ንብረት ላይ ይገኝ የነበረ ቤት በከፍተኛ ገንዘብ ተከራየሁ።ችግሬ ግን የሠለጠኑ ሴቶች ማግኘቱ ነበር።

እንዳሁኑ ሴቶች እኔው መርጬ አሠለጠንኳቸው።የፀጉር አሠራሩንም፥ ዳንሱንም አሠለጥንኳቸው።በዚያን ጊዜ ዳንሱም አለባበሱም ብርቅ ስለነበረ ገበያው ደራ።የዚያን ጊዜው ደንበኞቹ ሁሉ ከፍ ያለ ደረጃ ላይ ደርሰዋል።ተጫዋቾቹም ጥሩ ቦታ ላይ ነው ያሉት።ግማሾቹ ትልልቅ ቡና ቤት ከፍተዋል። ሌሎቹ ደግሞ ባለሺላ ሆነዋል።ይህንን መቼም ሁሉ ያውቀዋል። ለጉራና ራሴን ከፍ ለማድረግ አይደለም፣እነሱም አልፎ አልፎ ይጠይቁኛል።

እኔ ሳላሰልጥናቸው በፊት በየጣሰው ቤት ክራራቸውን ይዘው ኩር ኩር ያደርጉ ነበር።ያኔ ከሰል ተራ ወይም ቺንኮ ተራ ይሉታል።ቺንኮ የሚሉት ጣሊያኖች ነበሩ።ስሙኒ ማለት ነው።እኛም ወዲያም ወዲህ ብሎ ይበላል ቀንቂቲ አድባሯም ጥሩ ቢያፈራንም ኬቲ እያልን ስለ ከሰል ተራ እንጫወት ነበር።ታዲያ እኔም ሴቶቹ አሳዘኑኝና “ምን ትሠራላችሁ? ቀንጆ ናችሁ፥ታምራላችሁ።ኑ እኔ ጋ ዳንሱን ተማሩ።እኔ ቤት ስንቱ እንግሊዝ፥ ስንቱ አሜሪካ፣ስንቱ መኳንንት ይመጣል።እኔ ልውሰዳችሁ።”ስላቸው “እኛ ልብስ የለንም። አንቺ ጋ መጥተን ምን እንፈጥራለን?” ሲሉኝ “ግድ የለም።የኔ ጌጥ የኔ ልብስ አለ።” እያልኩኝ እወስዳቸው ነበር።እዚያው ፀጉራቸውን እየተኮስኩ፥ ኩሉን እየኳልኩ አሳመርኳቸው።ዳንሱንም በደንብ አስተማርኳቸው።

ወይዘሮ ሜሪ ያለፈውን ጊዜ በማስታወስ “ይኸውላችሁ እነሱኑ ለማሠልጠን ስል የፀጉር መተኮሻውን ካስክ (ቆብ) እራሴ ላይ እያደረግሁ በሸተኛ ሆንኩ።” አለች።ቀጠል አድርጋ ዘወትር ቅዳሜና እሁድ የኔን ቤት ያየ ግራ ይገባዋል።የሰው ብዛት ይህ ነው አይባልም።ረብሻ እንዳይፈጠር ሰባት ዘበኛ ነበረኝ።

ገና በጊዜ “አርቲስቶቹ ገቡ ወይ በስንት ሰዓት ነው ዳንሱ የሚጀምረው?” እያሉ ስልክ ይደውላሉ።ልክ ሦስት ሰዓት ሲሆን ቤቱ በሰው ይሞላል።በኋላም አርቲስቶቹ የውስጥ ሱሪና የጡት መያዣ ብቻ ለብሰው ብቅ ይላሉ።

አስቀድመን ዊሲኪ ጠርሙስ ውስጥ ትንሽ ዊሲኪ እናደርግና በሻይ እንበርዘዋለን።ቦዩን በደንብ አስጠንቅቄ ከሌለው መጠጥ ጋር አብሮ ይደረድረዋል።ሴቶቹም ሲጋበዙ ዊሲኪ እንዲሉና ሻዩን እንዲጠጡ አድርጋችዋለሁ።ይህንን የማደርግበት ምክንያት ተሳክረው ዳንሱን እንዳያበላሹት ነው።

ወንዶቹም ሴቶቹ አንድ ጠርሙስ ዊሲኪ ለሦስት ጠጥተው ለምን አይሰክሩም እያሉ ይደነቃሉ።ለመቅመስ ሲመጡም ቦዩን ጠቀስ እናደርጋውና በምትኩ ሌላ ጠርሙስ ያኖራል።ይህን የምናደርገው ሞቅ ካላቸው በኋላ ነው።

የዳንሱም አይነት የበዛ ነው፣ታንጉ፣ቫልስ፥ቤርዲሉና፣ማዙካ፣ቲፐታፕ፣ እነዚህን ሁሉ ዓይነት ጨወታዎች እንጫወት ነበር።ቤርዲሉና የተባለው ዳንስ ወንድና ሴት እቅፍቅፍ ብለው ፍቅራቸውን የሚወጡበት ነው።ዳንሱም የሚመራው በአረንጓዴ መብራትና በለስለሳ ሙዚቃ ነው።ማዙካ በውርርድ የሚጫወቱት ዳንስ ነው።በሻምፓኝ፣ በወርቅና በገንዘብ እየተወራረዱ ጫወታሉ።እኔ ከዳኞቹ አንደኛዋ ስለነበርኩ ፊት ለፊት እንቀመጥና ለረታው ሽልማቱን እንሰጣለን።

ለመጀመሪያ ጊዜ ቀይ-መብራት እሥራ ላይ ያዋልኩ ነኝ።እቤቴ ውስጥ የነበረው የመብራት አይነት ብዙ ነበር።ሁሉም ከየአቅጣጫው ፏ ብሎ ይበራል።የውጭ አገር ዜጐችማ ልክ የአገራቸውን እየመሰላቸው ይደነቁ ነበር።ይህንን ቀይ መብራት ዛሬ በየመንደሩ ተንጣሎ ሳየው በጣም ያናደኛል።ያኔ እንዴት ያምር ነበር።አትክልቴ ውስጥ ሳይቀር እንኳን መብራት አደርግ ነበር።

ታዲያ አሁን ሁኳም አንጠልጥላው ሳይ ያስቀይመኛል።በመጀመሪያ የተጠቀምኩበት እኔ መሆኔን የሚውቁ እግዜር ይይልሽ አንቺ ባትጀምሪው ኖሮ እኛም አንጠቀምበትም ነበር።አሁን ይኸው ለስድብ አዋልሽው እያሉ ይወቅሱኛል።

በኅላም ይህ ነገር በጣም እየተለመደ በመሄዱ አንዳንድ ሰዎች ተጋሩኝ። ማዘጋጃ ቤትም ፈፅሞ በውስጥ ሱሪና በጡት መያዣ ብቻ እንዳይደንስ ጥብቅ ትዕዛዝ አወጣ።ስለዚህም ረዥም ልብስ፥ ከላይ ክፍት የሆነ ብቻ ይለበስ ጀመር።ይህ በመጠኑም ቢሆን ገበያዬን ቀንሶብኛል።

እያደር ብዙ ሰዎች ቡና ቤትና ዳንስ ቤት ከፈቱ።ረብሻውም እየበረከተ ሄደ።ከተማው ውስጥ ድብድብ ሆነ።ስሞታውም በዛብኝ።ትኩራለች፥ሰው ትጠየፋለች እያለ ጉረምሳው ይዝትብኝ ጀመር።እኔም ልክ እንደሙሽራ እደበቅ ነበር።ይህቺ ሜሪ የሚኳት የቷ ናት እያለ ሁሉም ይወራረዳል።እኔ የምደበቅበት ምክንያቱ እኔን ለማየት ብቻ ገንዘባቸውን እየከፈሉ የሚመጡ ሰዎች ስለነበሩ ነው።መንግስት ሳይሾመኝ ልክ እንድ አንድ ሚኒስተር በአራዳ ውስጥ አዝ ነበር።

ቅድም እንደተናገርኩት እያደር ንትርኩ ጠቡ በመብዛቱ ትንሽ ተበሳጨሁ።ይህንንም ሥራ ለማቆም ወሰንኩ።ሠራተኞቼም እራሳቻችንን እንቻል ስላሉኝ ዳንስ ቤቱን ዘጋሁ።

ሌላ የገቢ ምንጭ ማግኘት ፈለግሁና ወደ ፀጉር ሥራው አተኩርኩ።ይህንንም ሥራ ለመጀመር ያነሳሳኝ አንድ ትልቅ ሰው ቤት ግብዣ ተጠርቼ ሄጄ የጋባዤ ልጅ ነጠላ ተከናንባ በአጠገቤ ስታልፍ ማየቴ ነው።በጣም ነደደኝ።ምክንያቱም ቀንጆ ሆና ሳለ በነጠላ

ተከናንባ ውብቷን ስላጠፋቻው ነው።ፈረንሳይቷ ጓደኞዬ የፀጉር ሥራ አስተምራኝ ስለነበረ ሱቅ ከፍቼ ይህንን ሁሉ ቀንጆ የባሰ ማስዋብ አለብኝ ብዬ ወሰንኩ።

የኛ ሴቶች ፀጉር እንደምታውቀው በደንብ የተያዘ አይደለም።ይህን አምበሬ ጭቃ ይለድፉና በዚህ በአበሻ ሚዶ ሲያበጥሩት ለጥ ብሎ ይተኛላቸዋል።አዳር ቤት ሲሄዱ የሰው አንሶላ ያጨማልቃሉ።በነሱ ቤት መሠልጠናቸው ነው።እኔም እየተመለከትኩ በግጥም እሰድባቸው ነበር።

***ያሠራሽው አልጋ ወፍራም አጣና ነው፣***
***ያነጠፍሽው ፍራሽ የሱሉልታ ሣር ነው፣***
***እግርሽ ከታጠበ ሰባት አመቱ ነው፣***
***የጠጉርሽ አቧራ ዓይኔን ሊያጠፋው ነው።***


ሜሪ አርምዴ

እያልኩ እነሱን በማንቋሸሽ ሥራዬን አስተዋወቅሁ።በዚህም ብዙ ደንበኞች አፈራሁ።የቻሉት ያኔውኑ ይሰጡኛል።ያልቻሉት ቀስ በቀስ እዳቸውን ይከፍላሉ።በዚህ ብዙውን አሠለጥንኩ።ብዙዎችም ጉፈሬአቸውን እንድከረክምላቸው ይለምኑኛል።ያኔ ወንዶቹም እንዲህ እያሉ ይገጥሙ ነበር።

***ጉፈሬ ክም ክም ጉፈሬ ክም ክም ሜማ ሲጥ ሲጥ***
***እኔ አላገባሽም ምኒልክ ይሙት፤***

አየህ የዚያን ጊዜ ጉፈሬ አንድ ሰዓሊ ተጨንቆ የሳለው ነው የሚመስለው።የዛሬውማ የዛር ውላጅ ይመስል ተንጨፍሮ ማስቀየሙ።የያኔው ሌላ ነው።በርሞሌ የሚባል ሽቶ ስለነበር እሱንም እሸጥ ነበር።

ካፒቴን ናልባንዲያን ነፍሳቸውን ይማረውና-ዲያቆኖችንና ድምፀ መልካሞችን አንድነት ሰብሰብው ያሠለጥኑ ነበርና፥ እኔንም በዳንሱና በልብሱ በኩል ነይና እርጂን ስለአሉኝ ማዘጋጃ ቤት ተቀጠርኩና ለአክተሮቹ የልብስ ሞድ በማቅረብ አገለገልኩ።ከዚያም ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ቴያትር ተዘዋውሬለዘጠኝ ዓመታት አገለገልኩ። የቴዎድሮስ ቴያትር ሲሠራ ሹሩባውን፥ አንዳንዱን ጌጥ፥ የሃኒባል ቴያትር ሲሠራ ልብሱን ያዘጋጀሁት እኔ ነኝ።ይሁን እንጂ እያደር ባየው የደመወዝ አበል ሳይሰጠኝ በነፃ ይህን ያህል ጊዜ ማገልገሌ ቅር አለኝ።በእርግጥ ቤቱ ብዙ ነገር አስተምሮኛል።ይህንን አልክድም።

ሜሪ ይህን ያህል ጊዜ ስትኖር የሕግ ባል እንደነበራት ለጠየቅናት መልስ ስትሰጥ “አንድ እንግሊዛዊ አግብቼ ነበር።ስሙ ጁሮምሉ ይባላል።ከእርሱ ጋር ብዙ ጊዜ ኖሬአለሁ።ግን ልጅ አልወለድንም።በመሀሉ ያቺ ፈረንሳዊት ወደ ጅቡቲ ይዛኝ ሄደችና ትዳሬ ፈረሰ።የማልዘነጋው ነገር ቢኖር የጁሮምሉ ሁኔታ ውለታ ነው።አልፈልግም ብዬ ወደ ጅቡቲ ስሄድ ብዙ ገንዘብ ሰጠኝ።ከዚያ ወዲህ ዓይን ዓይን አልተለያየንም።ከእርሱ ያፋታኝ ዋና ምክንያት የሰው አፍ ነው።ሜሪ ሐይማኖቷን ለወጠች እያሉ ሲያወሩብኝ እርግፍ አድርጌ ተውኩት።

ሜሪ አርምዴ ይህን ያህል ዘመን ስትኖር ምንም ቅርስ አላፈራችም።ሜሪ ያልሞከረችው ሥራ አልነበረም።ቀድሞ አራዳ ውስጥ ዝናዋ ያስተጋባውን ያህል ዛሬ በአንዲት አነስተኛ ቤት ተወስና የጥቂት ደንበኞቿን ፀጉር ትተኩሳለች።አልፎ አልፎ በሬድዮ ድምፅዋ ሲሰማ፣በቴሌቪዢን መስኮት ብቅ ስትል ብቻ አይ ሜሪ የሚሉ የጥንት ወዳጆቿ ናቸው።

እሱዋም በአሁኑ ጊዜ ከክራርዋ አብልጣ የምትወደው የላትም።ክራርዋ ከራስጌዋ በዥጉርጉር ቀለም ዘንጦ ተሰቅሏል።ሲከፋት ከተሰቀለበት አውርዳ ዘፈኗን ትነካዋለች።ባሌም፥ አባቴም ወንድሜም ክራሬ ነው የምትለው ሜሪ መከፋቷ እንዲታወቅባት አትፈልግም።ዘውትር መሳቅ ነው።ይሁን እንጂ በሕይወቷ ቅር የሚያሰኝ ዱብዳ አንድ ቀን የደረሰባት መሆኑን አወጋችኝ።

“ይኸውልህ ድህነቴን እያወቁ ጋዜጠኞቹ ጉድ ሠሩኝ።ውጭ ሀገር ያሉ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ከፍ አድረገው ዝናየን ለሚርያም ማኬባ ነግረዋት ነበር አሉ።ስማችሁም መልካችሁም ይመሳሰላል።ትልቋ የኢትዮጵያ አርቲስት እርሷ ነች።”ብለው ስለነገሯት እሷም እኔን ለማየት ትፈልግ ኖሮ፥ ለአፍሪካ ስብሰባ በመጣች ጊዜ ጋዜጠኞቹ እዚያች ደሳሳ ጉጆየ ይዘዋት መጡ።

ድሃ ነኝ ገንዘብ የለኝም በያት አሉኝ።እኔ ለራሴ ጥዩፍ ነኝ።እኔ ለራሴ ጥዩፍ ነኝ።ደሀ ነኝ ብላት ምናልባት አንድ ሺህ ብር ወይንም ያነሰ ነው የምትሰጠኝ።ግን ዞራ አይ የኢትዮጲያ አርቲስት ብላ ማለቷ አይቀርም።ለምን ልዋረድ? ሚርያም ማኬባ በቱርጅማን “ቤትሽ እዚህ ነው?” አለችኝ።ሰውነቴ ሽምቅቅ አለ።ምክንያቱም ጥቀርሻው፥ ሸረሪቱ እንኳ እንኳን ለእሷ ለሌላውም አይበጅ።ቶሎ አልኩና “የለም የኔ ቤት ይህ አይደለም።

ገረዴ ታማ ልጠይቃት መጥቼ ነው”። አልኩ።ገረዴ ሳትታመም በብርድ ልብስ ጀቡኜ አልጋ ውስጥ አስተኛኋትና እንድታቃስት ለመንኳት።እሷም እንዳልኳት ኸኸኸ ስትል ሚርያም ማኬባ አዘነችና አምሳ የአሜሪካን ብር አንስታ “እንቺ ስጫት” አለችኝ።እኔም ያቺን ብር “የኔ ገንዘብ ነው በኋላ ትሰጭኛለሽ”። ብዬ ትራስዋ ሥር አስቀመጥኩ።በኋላም ቤትሽን አሳይኝ ብትለኝ ቀዳማዊ ኀይለስላሴ ቲያትር አጠገብ ያለውን የበድሉን ሕንፃ የኔ ነው ብዬ ነገርኳት።ለቱርጁማኑ እናትና አባቴ ስለርስት ጉዳይ ንትረክ ይዘዋልና ፀትታ እነነሳቸዋለን።እሁድ እራት ጋብዤሻለሁና እንዳትቀሪብኝ።አልኩና ተሰናበትኳት።

ግብዣውን የት አባቴ እንደማዘጋጅ ግራ ገባኝ።ምን ይዋጠኝ? ምነው ያችኑ አነስተኛ ቤት የኔ ነች ባልኩ ፥ እያልኩ ስጨነቅ አንድ የማውቃቸውን ከፍተኛ ስልጣን ያላቸውን ሰው ላስቸግር ወሰንኩ።እቤታቸው ሄጄ እግራቸው ላይ ወድቄ አለቀስኩ።ታሪኩንም ዘርዝሬ ነገርኳቸው።እሳቸውም በነገሩ ተደንቀው፥ ደግሰው፥ቤቱን በደንብ አድረገው አዘጋጁልኝ።ከዚህም ሌላ ሚርያም ማኬባን ከሆቴሏ የሚመጣት መኪናና ሾፌር ሰጡኝ።እኔም የእሳቸውንና የባለቤታቸውን ፎቶግራፍ ከግድግዳው ላይ አንስቼ የኔን ፎቶ አደረግሁ።የራሴ ቤት ለማስመሰል ፒጃማ ለበስኩ።ልክ እንደቤቴ ሸር ጉድ እያልኩ ጋበዝኳት።ሾፌሩንም አስቀድሜ ለምኜው ነበርና ከእራት በኋላ እሷን ለማድረስ ስንወጣ ወርዶ እጅ ነስቶ፣መኪና ከፍቶ አስገባን።ሆቴላም ስንደርስ ሮጦ ወጣና ከፈተለን።

በመጨረሻም የሀገር ልብስ ጥሩውን በርካሽ ዋጋ ገዝቼ ሸለምኳት።እሷም ቀንጆ የደረት ጌጥ ሸለመችኝ።እባክህ ጌታዬ አታጋልጠኝ ብዬ ለቁልቢው ገብርኤል ጥላና ጧፍ ተስዬ ነበር።ሳልጋለጥ ቀረሁ እልሃለሁ።

ባይልልኝ ነው እንጂ እኔም ቢጠሩኝ የማልሰማ እመቤት ነበርኩ፤ምን ያደርጋል እጄ አመድ አፋሽ ሆነ።"አለች እንባዋ አቅሮ መሬቱን እየቀረቀረች።

ብስጭቴን፣ምሬቴን፣ችግሬን ፍቅረኞቼን የማስታውሰው ከክራሬ ጋር ስሜት ሲይዘኝ ነው።አለችና ክራሯን ደረደረች።



እስቲ ጠይቁልኝ ሚስቲቱን በሰው፣ባሏ ልቤን ወስዶ የት አደረሰው?

ዛፍ ያጣ ጉሬዛ አዳኝ ያበረረው የማትሆነኝ እንደሁ ልቤን ተው ልበለው

ጉጃምና ጉንደር ማዶ-ለማዶ ነው ፍቅር ያለ ቦታው አባ-ጨጓሬ ነው።

ዋይ ብዬ ልለይህ ዘመድ እንዳረዱት፣ሰቀቀን ነውና የሩቅ ሰው ቢወዱት
ተበድዬ ኑሬ አንጀቴ ተቃጥሎ

አንጀቴ ተቀርጦ

ስቃጠል ከርሜ

ዳግሚያ ሰው ወደድኩኝ ልብ የለኝም እኔ።

ወዘፍዘፍ ያለ ነው የግራር አጥር፣

እኔ ለጅል ፍቅር እምብዛም አልጥር

ሸህ አባድር መጀን አምስቱ በረኛ፣

አዙሮ አዙሮ ይጣልህ ወደኛ።"

*ምሥጋና፣*

- ✓ ንመጽሔት መነን፣ንዝተፈላለዩ ጋዜጣታት
- ✓ ንቤተ መዘክር ኣዲስ ኣበባ፣
- ✓ ንወነንቲ ትካላት ኣብ ፒያሳን ደቂ ፒያሳ ነበርን፣
- ✓ ንኣቶ ኪሮስ ወልደሚካኤል፣ወ/ሮ ለምለምን፣
- ✓ ኣስማቶም ዘይተገልጸ ዝተሓባበሩ ዘበሉ ኹሎም እብል።